# ታሪክ አዋቂዎች አለቁና የታሪክ ደንቆሮዎች ታሪክ ሲጽፉ

ከአቻናፊ አራጋው--ምንሽር

ማን ይናገር የሚያውቅ የነበረ ማን ይቀላምድ የማያውቅ ያልነበረ። ዛሬ ዛሬ እማ እውነት ቀጥና ከስራ ብቻዋን ቀርታ አልሞትም ባይ ተጋዳይ ሁና እውነትን ገደልነ ብለው ቢቀብሯትም ዕውነት ተቀብራ አትቀርም። መቃብሩን ገልብጣው ትወጣለች። ያኔ የዛን ቀንማ የታሪክ ደንቆሮ ደላላ ታሪክ አይንዋን አፍጣ ጥርስዋ አግጣ ወፍራ፣ ደጉሣ፣ ሥትመጣ በባርጤዛና በሰራቂያን አይኗ ሥታይህ ሁሉ ነገር ትቢያ ትቢያ ሲሸት የገዛ ቀፈትህ ሰንጎ ይዞ መራመድ ሲያቅትህ እውነት ወፍራ ደምቃ ውሸት ቀጥና ከስራ ሥታያት ዛሬ በውሸት ያወቅኸው ታሪክ ነገ በእውነት የማታውቀው ታሪክ ሲሆንብህ ገብረሆድ ምን ትል ይሆን <u>ገብረሆድ </u>ዛሬ አውነት መናገር ጨዋነት አይደለም

ዛሬ ለአገር ለህዝብ አንድነት፤መታገል ኋላቀርነት የምትለኝ

ነገ የአገርም የህዝብ አንድነት ሲከበር

***ወያኔም ይሄድና ገንዘቡም ያልቅና***

ገብረሆድ ያስተዛዝበና ይህ ቀን ያልፍና

አንበሳው አረጀ መሰል የጠነባ ስጋ ይዞ ውሻው አስፈራው። ነገሩ አንበሳው አንበሳ እንጅ ውሻ እንደማይወልድ እሳት ከነበረበትም እረመጽ እንደማይጠፋ የባንዳ የልጅ ልጅ የባንዳ የልጅ ባንዳ እንጂ ጀግና አይሆንም። ባንዳ መወሸከቱን መቀላመዱን ያቁም። ዥንጀሮ በአንበሳ መፈከሩን ያቁም ሗላ የደንቆሮና እውር ሠርግና ጭፈራ እንዳይሆን በሆዳችሁ ከማሰብ በአእምሮአችሁ እስቡ ብረት ከተመአዘዝነ ገላጋይ አያቆመነም።

ባለፉ 32 ዓመታት በኢሕአፓ ላይ ያልተፃፈ የሐሠት ድርሰት አልብረም አሁንም አልቆመም ፀሀፊወችም ለተወሰነ ጊዜ በድርጅቱ ውስጥ በአመራርነት እንዲሁም በተራ አባል የነበሩ በሥነ ልቦና በሥነ ምግባር ብልሹነት ብቃት ማነስ የተባረሩ የድርጅቱን ገንዘብና መሣሪያ ሰርቀው እንዲሁም በአይደሎጅ ክህደት ከድርጅቱ የከዱ ናቸው።ከዚህ ላይ የድርጅቱን አመራር በመሥመር ልዩነት ተከራክረው ሊያሣምኑ እነሱም ሊያምኑ ስላልቻሉ ከድርጅቱ ተሰናብተው የሄዱ የሉም ማሌቴ እዳልሆነ ይያዝልኝ በመሥመር ልዩነት የሄዱ ጓዶች የሀስት ድርሰት ሲጽፉ አይታዩም። ለጠላት ገብተው አላገለግሉም አያገለግሉም። ነገር ግን ከድርጅቱ በሥነ ልቦ በሥነ ምግባር ልሸቀት ንቅዘት ምክንያት ከኢሕአፓ\ኢሕአሠ

የተባረሩ፣ ከድተው ንብረቱን ዘርፈው የሄዱ ግለሰቦች ቀድሞ ከደርግ አሁን ደግሞ ወያኔ ጋር ሆነው የዛን ትውልድ ታሪክ ለማጥፋት ያልፃፉት የማይፅፉት የሀሰት ድርሰት አልነበረም፣ የለምና ውሸት ሲደጋገም እውነት ሲለሚመስል ዝምብሎ ማየቱ መቆም አለበት። ስለአለፉት የተረፍነው ታሪካቸው የመከላከል የማስከበር ሀላፊነት ኣለብን። የሀሰት ድርሰት የፃፉትንም ለወደፊቱ የሚፃፉትን ከፅሑፉ እስከ ፀሀፊዎች ምንነት ማንነት ማጋለጥ አለብን። ለምሳሌ ለወደፊት የሀሰት ድርሰት ለመፃፍ አቅዶ ያለው የቀድሞው የኢሕአፓው የጎንደር ዞን በሀቢቡ ታከለ ወይም በቀዋስ ወይም በአማኑኤል ና በደማስ ወይም አምሃ እንዲሁም ሌሎችም ያሉበት እኔ እስተማውቀው የተፃፉት የሀሰት ድርሰቶች በትቂቱ፤

1. ይድረስ ለባለታሪኩ በሚል የተፃፈው የታሪክ እቆቅልሽ አንድ እውነት አሥር ውሸት ለውሸቱም መረን ሳይዝለት ለመፃፍ እንደ መረጠ አይገባኝም።ፀሀፊው ማን እንደሆነ አውቃለሁ ሥሙን ከመጥራት ልቆጠብ ወደ ሻቢያ ወይም ወደ ወያኔ እንዳይወግን እውነት ህሊና ላለው ሰው ለዝንተአለም ቀላል ነበረች ለዘላለም ቀላልነች በማንኛው ጊዜና ቦታ ቢሸከምዋት አትከብድም ህሊና ለሌው ሰው ውሸት ቀላል ናት። እውነት እጅግ ከባድ ናት ጸሀፊው የጻፈው ደርግና ፀረ ኢሕአፓ ሐይሎችን ለማሥደሠት ነበር።
2. ከፀረ-ኢትዮጵያው ከፀረ-አማራው ከፀረ-ዐብዮቱ ለከተማው እልቂት ከወያኔና ከደርግ ጋር እኩል ተጣያቂው አህያ መጣች ተጭና ዳቦ ደርግ እስከ ሀምሌ አቦ አንድ ሀሙስ የቀረው መንግሥት እያለ ለከተማው እልቂት ተጨማሪ ሀይል የነበረው የሞረተው ተወላጅ በክፍሉ ታደሰ የተፃፈው ያትውልድ ክፍል ፩ና  ክፍል፪ በሚል የተፃፈው የሀሰት የክደት ድርሰት ገቢያ አውጥቶ ሽጦ ለመከበር ነበር።ክፍሉ መፅሐፉን አልሸጠም መፀፉ ግን ክፍሉ ታደሰን ገቢያ አውጥቶ ሁለመናው ግልጥልጥ አድርጎ ዘርግቶ አእምሮው ለሥም ለገንዘብ ለሥልጣን ሲል እንደጋጀ እንደሚጋጅ እንደዘገጠ እንደሚዘግጥ አሳይቶ ሽጦታል የታሪክ እውር የታሪክ ደንቆሮ የታሪክ ሽፍታ ማለት ክፍሉ ነው።
3. የደም ዘመን በሚል የተፃፈው በታከሎ ተሾመ ደግሞ ሥም ማጥፋትና ክህደት ውሸትን ከመርሻ ዮሴፍ የወረሰው ደዌ ነው፣ በድለላ ሽርክና የተፃፈ ድርሰት ነበር ምን  ያህል ገንዘብ እዳመጣላቸው የሚያውቁት መርሻና ታከሎ ናቸው ወያኔ ግን በአገር ቤት በብዛት አሰራጭቶ ነበር መርሻና ታከሎ ለማጥቃት የሞከሩ ጓዲት አሰለፈች ወይም ማዘር ጭምር ነው ማዘር በጭሆት እጅዋን አውታ ሚስጥር አለኝ ልፈናዳነኝ ልናገር ብላትጮህ የመናር እድል ተሰጣት መርሻ ስልክ ደውሎ ድርጅቱን አፈርሰው ዕናፈርሠዋለን ብሎ ስለገረኝ ተጠንቀቁ ድርጅቱን እንዳያፈርሰው ብላ ተናገረች ተሰብሳቢው አዝኖ አሳፍሮ አስቀመጣት በተለይ ወጣት እሴት በወቀትም

በእድሜም ያልታደለች አሉ ገጽ 346። እደዚህ የሚያስቡ የኢሕአፓ አባላት አሉ ነበሩ ብሎ ለመቀበል ይከብዳል።ግን አንተና መርሻ ለተለያየ ተግባር ከአልፎ ሀጅ እህቶቻችን የታጋበዙ ይሆናሉ እንጂ የኢሕአፓ አባል ሊሆኑ አይችሉም ነገር ግን ያንተው ጭንጋፍ ጭቅላትና የመርሻውም ወራዳ እርኩስ ጭቅላት ቢደመር ከማዘር ከኮቲዋም አትደርሱ።የማዘር ታሪክ በወርቃማ ለዘላዓለም በማይደበዝዝ ቀለም የተጻፈ ስለሆነ ለማጥፋት መሞከር ራሱን የቻለ ርካሽነት ና ወራዳነት ነው። ስለሠራዊቱ ስለኢህአወሊ፣ስለከተማው ትጥቅ ትግል ካንተ የበለጠ የጎንደር ዝንጀሮወች ውሻ ድመቶች እውቀት አላቸው።

4. ሁለት ፅሁፎች በአፅብሃ ወይም በአያሻረው ወይም አስማማው ሐይሉ ዓጉል ኢሕአሠና እንዴት ተበተንን የሚሉ ጽሁፎች አስገራሚነታቸው ሰው ሁኖ በመፈጠሩ አለማፈሩ ብቻ ነው የሚገርመው።መቸም በአሁኑ ጊዜ የምርጥ ዘር መሆን ሳያውቁ ያሳውቃል። ሳይኖሩ ነበሩ። እኔ እኔ ማለቱ አይከብዳቸውም። የትግራይ ፖሊሥ ሙሑር የወያኔው ጀሮ ጠቢ የነበረው አሁንም የሆነው በኢሕአሠ ተማርኮ ለተወሠነ ወራት ከሠራዊቱ ጋር የተንቀሳቀሰው አጽብሃ አያሻረው ወይም አሥማማው ሐይሉ ሥለሠራዊቱ ታሪክ ለመፃፍ የእውቀቱም የስነ ልቦና የሥነ ምግባር ብቃት ፈፅሞ የለውም። ነገር ግን ጠይቄ ነው የፃፍኩት የሚለው እውነት ከሆነ በተለይ የሁለቱ ሮባና ጅግሣ የኢሕአሠን ታሪክ አስማማው እንደ ፃፈው ከሆነ የሚያውቁት ታሪክ ነው ብለው ከነገሩት ትላንት የመራችሁን ያን ጀግና ሠራዊትም የመራችሁት በጠላትነት ነበር ማለት ነው።

እንፃፍ ከተባለ እኮ ሮባ ስለ ድብ ባህሩ ውርደት ና ስለአርባያው አንተ ስለሥቀሰልክበት ጦርነት ድክመትና ቅሌት መፃፍ ይቻላል።ነገር ግን ከፊታችን አንድ አጥር አለ ያን አጥር ከተዛለልን ገላጋይ አያድነነም ያለን አማራጭ ያን ታሪክ ማክበሩ መጠበቁ ነው።ዛሬ ኦሮማይ ቆዳ ለብሶ ከምርጥ ዘሮች ጋር ሁኖ ያን ታሪክ ማራከስ ማዋረድ በእኔ እምነት ወራዳነት ርካሽነት ነው።አስማማው ስለሠራዊት ነገሩኝ የሚላቸው ሮባና ጅግሣ ብቻ አይደሉም ፀጋየ ዳጉሣንም ክፍሉንም ፀሀየን እንዴት መርሻን እደዘለለው ነው የማይገባኝ ፀሐየ በሠፊው ከመጻሐፉ ውስጥ ስሙ ተጠቅሷ የምርጡ ዘሮች ተደጋግፈው ይሆን ይህን ውሸት የፃፉት።?

መቼም የማያውቅ ሰው አደፋፈር ስለብተናው አስማማው መጽሐፍ ጽፏል። ለምርጥ ዘር የሚሣነው ነገር የለም። ብጾት ሳያውቅ የወቀ ሳይሰማ የሰማ ሳይኖር የነበረ ሳያይ ያየ ነው።ስለብተናው ለመፃፍ የስነ ምግባር የስነ ልቦና ብቃት አለኝ ብሎ ማሰቡ ምን ያህል ጠላት እንደ ነበር ና የጠላት ጀሮ ጠቢ እንደ ነበር ነው። ብተና

የተካሄደው አስማማው ለደርግ ጎንደር ክፍለ ሀገር ድብረታቦር አውራጃ እጁን ሰጥቶ እስር ከገባ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው።አስማማው ድብረታቦር እስር ቤት ታግቶ እያለ ከታገተበት ሁኖ ብተናው ተሳተፈ ወይም ልዩ የሚከታተልበት መሳሪያ ነበረው ማለት ነው። ነገር ግን የሚያውቀው ተበታኙ እንጂ በታኙ አይደለም ርጂን 3ን የበተኑት ያሬድ ያዕቆብ፣ ካሱ ይላላ፣ አንበርብ ወይም በረከት፤ አዲሱ ለገሠ፤ ታምራት ላይኔ፤ እንዲሁም ሌሎች እንዲሁም ርጅን 2ቱን የበተኑት ሠራዊቱን አምዴ፤ ገብሬ ጭላዳ፤ ክፍሉ ታደሰ፣ ሠሎሞን ገብረ ስላሴ፣ ደሳለኝ፣ አንበርብር፣ አሊጋዝ፣ ይመር፣ ጌራ፣ ጸሐይ፣ ሡብለ፣ ዳኔል፣ በጠቅላላው የኳድሬው አመራር አባላት መሆናቸውን ኣታውቅምን? ዎይስ ለአባሻ ለስም ለቅጥረኝ ስትል ነው ያልፃፍከው።እንዴት ነው።

አያሻረው የአማረኛ ግድፈት ነው እንዴት ተበተን ስትል አታፍርም አንተማ ከመጀመሪያውም ከኛ ጋር አይደለህም። የኛ አልነበርህ። በእኔ እምነት ለዛኛው ጎራ ለምርጥ ዘሩ ጎራ ጀሮ ጠቢ እንደ ነበርህ ነው የምረዳው። ተግባርህ የሚያሳየኝ ለዚያ ነው። አያሻረው የሚለው ስም የተሰጠህ። ሻረው ማለት ሰርዘው፣ ካደው፣ አስበላው፣ ማለት ስለሆነ ከከሃዲ እንደ ዚህ ያለ ክህደት የተጠበቀ ነው። የሚጠበቅ ነው።

5. የክደት ጽሑፉ በመጽሀፍ መልክ የቀረበው በአበሻይቱ ፈረጅ በህይወት ተፈራ Tower in the Sky በሚል ስለጌታቸው ማሩ ነው በዋናነት ያተኮረው። በ1969 ዓ.ም. ኢሕአፓ ሀናለ ብሎ ስለአንጃዎች ያወጣው ወረቀት ነው እንደ መረጃ የሚቀርብ የነበረው ወረቀቱ እንደ ወጣ ጥያቄ አቅርቤ ነበር የጌታቸው ማሩ ሁኔታ አንጃነት ነው ወይስ የህሳብ ልዩነት ነው?እስካሁን ድረስ መልስ አላገኘሁ ነገር ግን የጌታቸው ፍቅረኛ የነበረች መፅፍኛ ፃፈችን ሥሰማ ለጥያቄየ መልስ ትሰጠኝ ይሆን ?አልኩ ከፍራቻ ከጥርጣሬ ጋር ነው።የፍራቻየ የጥርጣሬየ የመነሻ የሆነው ፍቅረኛ ነበርኩ ነበረች የሚለው ቃላት ነው ወይዘሮቱ የፃፉት እውነቱን ወይስ የውሸማ እልቅስ ነው በሚል መጽሀፉን ፍለጋ ገባሁ አገር ቤት ጓደኞቸ ላኩልኝ መጽሐፉን ከማንበቤ በፊት ክፍሉ ታደሰ ብዙ ምክ ና መረጃ ሠጥቻት አለሁ ብሎ ያሥወራ ስለነበር ከውሸማ ልቅሶነት አልፎ የቅጥረኝ ሸክም ሳይኖረው እንደ ማይቀረው ገምቼ መጽሐፉ ማንበብ ጀመርኩ እስከ ምጨርሥ በእንሊዛሽ ኮራሁበት ነገር ግን 99.8 ከመቶው የኢትዮጵያ ህዝብ እንግሊዘኛ አያነብም ልፋትሽ ድካምሽ አንቺ ጽፈሽው ከሆነ ልፋትሽ ድካምሽ ውሃ በልቶት ቀረ ማለት ነው ምናልባ አማርኛ ቋንቋ የጠላት ቋንቋ ነው ከሚሉት ወገኖች ልትሆኚ ትችያለሽ ነገር ግን 99.8%ቱ የኢትዮጵያ

ህዝብ እውነቱን ማወቅ ማንበብ ይፈልጋል።አንች እንዳልሽው ትልቅ ህንፃ በሰማይ ላይ የለም በሰማይ ያሉ ሁለት ቦታዎች ናቸው ገሃነበሳት ወይም ገነት።ገነትን የሚያገኟት ሥለዕውነት እውነቱን የተናገሩ የተከራከሩ ናቸው ለገንዘብ ብለው ከዘር ጥላቻ ከድርጅት ጥላቻ ከአገር ጥላቻ ለቅጥረኝነት ተነስቶ እውነትን የካደ ጉግ ማጉግ ወደ ገሃነበሳት ነው ተወርውሮ የሚጣለው ከተሳሳቱም 99.8%ቱ ጋር መሳሳት ወርቅ ወርቃማ ስህተት ነው።

6. ሌላው የሐሡት ድርሰት የዘር ጥላቻ ያዘለ ክህደትን ቅጥረኝነት የተሸከመ በመጽሀፍ መልክ የቀረበ አሲምባ ፍቅር በሚል ነው። በወያኔው ጀሮ በነበርው ካሕሳይ አብርሃ ነው። የዛላ አንበሳው ተወልጀ ደካማ አርሶ አደር ነው። ምንም አብረን ብንታገል ብንቆስል ብንደማ ብንራብ ብንጠማ ቆላ ብንዎርድ ደጋ ብንወጣ ለህይወታችን ዘብ ብንቐቐም። ጥቃት የመጣለት የምርጥ ዘሮች ከኛ ጋር አይደሉም እንደማይሆኑ የአሲምባ ፍቅር ድርሰት ጸሀፊም አንዱ ምስክር ነው። የሁለት ጠንካራ ጓዶችን ታሪክ ከምርጡ ዘር ባለመወለዳቸው ከባንዳ ቤትሰብ አለመወለዳቸው የአድዋው ድል የአማራ ወረራ ኣለማለታቸው ንጹህን ስማቸውን ንጹሁን ታሪካቸው ለማጥቆር ለማጉደፍ ሞከረ። የአበበ ደብተራው ታሪክ ሥም እንኳስ ያ ትውልድ ገና የሚመጡት ትውልዶች እንደሚኮሩበት አልጠራጠርም። ማንም በማያደበዝዘው ወርቃማ ቀለም ተጽፎ ጽፎት ለማንኛው ጀግና የአበበ ደብታራው ታሪክ የጀግንነት የታሪክ ሥጦታ ነው። በእግጥ የአበበ ደብተራው ታሪክ ለገብረሆዶች ለባንዳዎች ለደም እንጃ መቅሰፍት ነው።ለምሳሌ የወያኔው ያነሳቸው ክሶች ፩--የአበበ ደብተራው ሽጉጥ ጠፍቶ ሽጉጡን ለመፈለግ እስኳድ ወደ ከተማ መላክ ፪--የድርጅቱን የሰራዊቱን ሚስጥር የያዘ ወረቀት አበበ ደብተራው ለአንድ ምክትል ጋንታ መሪ መስጠት ፫--አበበ ደብተራው የሰራዊቱ ህግ ጥሶ የተሰጠው መሳሪያ ለአንድ ተጋዳይ ለማስታዎሻ መስጠት ደንቆሮ ሰው ደፋር ነው ይባላል ስም ለማጥፋት ስለተቀጠርህ ስተከፈለህ እንጂ አበበን አታውቀውም።

ሌላው ካሕሳይ አብርሃ በአእምሮህ ስለህ ያስቀመጥሃትን ቬረሙጣይቱ ድላይ በሰራዊቱ ውስጥ የነበሩ ጓዶች አያውቋትም እኔም የአንተዋን ድላይ አላውቃትም እኔ የማውቃት ድላይ ለማንም ለምንም የማትበረክከዋን ቡከኑን በሰደፍ ፈሪውን በአፈሙዝ የምትገፋዋን ጠላትን በጥይት በሳንጃ የምትደፋውን ነው የማውቃት ድላይ ስሟን የምታጠፋው ድላይ ፈሪ ቡከን አትወድም አስራ ገርፋህ ይሆናል።

ሌላው በወያኔ ሻቢያ እና በኢሕአሠ መካከል ተደርገው ስለነበሩ ጦርነቶች ወያኔ

ሻቢያን የድል ባለቤት ደፋር ጀግና ተብሎ መቅረቡ እውነትን አለመፍራት አለማፈርህ ያንተውስ ዘረኝነትስ መረንን ያለፈ ከናዚዎች ከፋስሽቶች ከሳይንቲስቶች በላይ ነው።ነገሩ ልክነህ አንተና አንተን መሰሎች የወያኔ ሻቢያ ጀሮ ጠቢዎች ከሠራዊቱ ውስጥ ስለነበራች የኢሕአሠን እንቅስቃሴ ያውቁ ነበር እነሱ የኛን ጓዶች ሲይዙ ይገሉ እኛ የማረክነው የወያኔ ወታደር የያዝነው ሰላይ ምሳውን አብልተን ለራቱ የሚሆን ስንቅ ሰጥተን እንድንሰድ ጠ.አ.ኮ ያስገድደን ነበር። የተከበበ የተምበረከከ የወያኔ ሻቢያን ወታደር ጠ.አ.ኮ በሌባ መንገድ በጠፍ ጨረቃ እየመራ እንዲ አመልጥ ያደርግ ነበር ለዛም ነው ከወያኔ ጋር በተደረጉት ጦርነቶች ጠ.አ.ኮው አለመታመኑ ከዛም የወሎው ክስረት የበለሳው እልቂት የድብ ባህሩ ውርደት ተደረባብረው ጠ.አ.ኮው ይውረድ የሚለው ጥያቄ የተነሳ ጠ.አ.ኮው ከስልጣን ወረደ በምትኩ ጊ.አ.ኮ ተቋቋመ ጊ.አ.ኮው ሠራዊቱ በተነው

7. በደም ረጋጮች፤በቁም ሙታን በሰሎሞን ጊ.አ.ኮ በደሳለኝ ወይም ዶክተር ዜሮ ዮሴፍ መርሻ የሚመራው እራሳቸው ከእየሱስ እንዲሁም ፃድቃን ጋር አወዳድረው አቡኔ የባለዛር ጠንቋይ ሁኖ ጾዳለና መንግስቱ መስፍን አጉሪ ነሲቡ የጓዶችን አጽም እንደ ቄጠማ ነስናሽ አክሊሉ እጣን አጢያሽ ለይኩ ድቢ መች፤ሁነው ታይቶና መቃብር ፈንቅለው ልንነሳነው የሚለው የቁም ሙት ቡድን ነው።በቁሙ የሞተ በቁሙ የበደነ ሁሉ ግባ መሬት ይገባ እንጅ ያዉም መሬት እርኩስ ነህ ብላ ካልተፋችው በስተየቀር።የሰረቀ የቀጠፈ በሀሰት መሰከረ ጓደኛው የገደለ ያስገደለ የአገርና የህዝብ ክብር የሸጠ የለወጠ ድርብርብን ሞትን የሞትን እርኩስ ሞት ይሞታል እንጂ እንደ እየሱስ ከመቃብር ተነስቶ ተንሳየ ብርሃንን ለማየት እድሉም ሆነ ስራው አይፈቅድለትም ነገር ግን የበላው ገንዘብ የዋሸው ውሸት ሥላለ ልነሳ ነው እያለ መናዘዙ የተጠበቀ ነው ግን ሙት ይዞ ይሞታልና መጠንቀቁ አማራጭ የለለው ምርጫ ነው።እግዜአብሄር ጥሩ ነው ሠማይና ምድርን አራርቆ ነው የፈጠረ በባንዳ እልቅሶ አይረበሽ።

8. ሌላው አስገራሚው ባይታውሩ ቡድን ለርማት እንቅስቃሴ ነኝ የሚለው ነው የሚሄድበት መንገድ ጠፍቶ እንዲጫወት የተፈቀደለትን ቁማር ዘሀር አልቀናው ብሎ እስከነ ጆኮሩ ተበልቶ እያሱና አሰፋ ናቸው ያስበሉኝ እያለ ደመ ነፍሱ የሚዳክረው ቡድን የርማት እንቅስቃሴ የሚጠላ የለም ስሙ ጥሩ ነው የተነሳበት ዓላማው ግን ለማያቅሽ ታጥበሽ ቅረቢ እላለሁ።በመጀመሪያ ዕርማት እንቅስቃሴ ማለት የማርክስዝም የሌኒንዝምን መርህ የሚከተሉ ድርጅቶች የድርጅታቸው ጥንካሬና ድክመት የድርጅቱን አባላትንም ስነልቦናዊ ስነምግባራዊ ብቃት ንቃት ንቅዘት ድክመት የሚገመግመበት መሳሪያ ነው።የዕርማት እንቅስቃሴው የድርጅቱ ጠንካራና

ደካማ ጎኑን ገምግሞ በጠንካራ እንበርታበት ብሎ በደካማ ጎኑን እንዲታረም በጥናት የተደገፉ መረጃና ሃሳቦችን ለኮንግረሱ ያቀርባል።ነገር ግን በዕርማት እንቅስቃሴ ጊዜ አባላት ከላይ ወደታች ከታች ወደላይ ይገመገማሉ በግምገማው ጊዜ የስነምግባር የስነልቦና ንቅዘት ብልሹነት ድክመት ላይ የወደቀ የአመራር አባል ከተገኘ ከስልጣን ያወርዳል ነገር ግን ከድርጅቱ የማባረር መብት ያለው ተራ አባላት ከሆኑ ግን ለዕርማት የተሰበሰበው አባላት ለድርጅቱ እንዲሁም ለአባላት ደህንነት አደገኛ ነው ናት ብሎ ተሰብሳቢው ካመነበት ከድርጅቱ የማባረር መብት አለው።ኮንግረስ ሁለት ግለሰቦችን ለመገምገም ለመክሰስ ኮንግረስ ሆነ የዕረማት እንቅስቃሴ አይጠራም ይጠራልኝ ለማለት አይቻልም ይጠራልኝ የማለት መብት ያላቸው የአባልነት ግዴታን የተወጡ አባላት ብቻ ናቸው።ከኮንግረስ ለመሳተፍ በአባላት መወከል የግድ ነው የአባላትን ውክልና ይጠይቃል።

ኢሕአፓ የግራ ፍልፍናን መከተሉን ትቶ ሶሻል ዲሞክራት ነኝ ካለ 27 ዓመቱ ነው። የርማት እንቅስቃሴ የሚለው ቡድን 27 ዓመት በሙሉ ኢሕአፓ ሶሻል ዴሞክራት ነው እያሉ ሲሰብኩ የነበሩ ግለሰቦች ቡድን ፈጥረው የዕርማት እንቅስቃሴ በሚል ቅጀት የተነሱት በዱላ በጉርሻ ነው። ለትግል ወይስ ለክህደት ነው? ሶሻል ዲሞክራቶች ሁሉ ነገር የሚወስኑት በኮንግረስ ነው ከኮንግረስ ለመሳተፍም የአባላትን ውክልናን ይጠይቃል።በእኔ እምነት አገርን ሀይማኖትን ጓደኛን ለፍርፋሪ ጉርሻ መለወጥ ዘለዓለማዊ ወራዳነት ነው።ገብረሆዶች ለክብር ቦታ የላቸውም ክብራቸው ክብሩ ያባቱ ቤት ሲዘረፍ አብሮ ያልዘረፈ ያገሩን የወገኑን ክብር ካልሸጠ ካላዋረደ 21ኛው ክፍለ ዘመን ፖለተከኛ አደለም የጭዋ ፖለቲካ አይከተልም ነው። እውተኛ ታጋይ ከ21ኛው ክፍለ ዘመን ወደ አንደኛው ክፍለ ዘመን ይመልሱ እንጂ የአገሩና የወገኑ ክብር አይሸጠም ።

ታጋይ ለትግል ሲነሳ በትግሉ ላይ ፍጹም እምነት ይዞ ነው። ከመጀመሪያው ትግሉ ያንተ ከሆነ አንተም የትግሉ ከሆንክ ውሃ በወፈረ ጊዜ ልትታገል ውሃ በቀጠነ ጊዜ ትግሉን መካድ ከመጀመሪያው ታጋይ አልነበርህም። የትግሉ ትሪስ እንጂ ታጋዩና ትግሉን ከሚታገሉ ባንዳዎች ገብረሆዶዎች ወደው ተማራኪዎች ደም እረጋጭ አንጃዎች ጋር በጥራት ታጋዩ መለየት አለበት። ታጋዩ ትግሉን ካላጠራ ከማንም ቆሸተ ድውይ ጋር ሁኖ መታገል አይቻልም።ሁልጊዜም ለታጋይ የሚያዋጣው ከብዛት ጥራት ነው። ጥይት ሳይተኮስበት ወዶ የሚሞትና የሚማረክ ወታደር ይዞ ጠላትን መግጠም አይቻልም።ባልታሰበ ጊዜ ሙቶና እጁን ለጠላት ሰጥቶ ትግሉ ያስመታዋል ታጋዩንም ይጎዳል።በመርሻ የሚመራው አንጃውና ባንዳው ሽማግሌ

መልምሎ የተመለመሉት ሽማግሌዎች የተወሰኑት ሠራዊቱን ከበተኑና ከድርጅቱ ከወጡ በኋላ በውጭ አገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር መዋቅር ውስጥ ተቀጥረው ከሚሰሩና ከኢሠፓ ካድሬዎችን መልምለው ጠንካራ ኢሕአፓ አባላትን እንደ ነሱ ባንዳ እንዲሆኑ አሸማግሉ ብለው ልከዋል።ግን ነገሩ አሳውን ለመያዝ ባሕሩን አደፍርሰው ነው። ወይም ከፈገግታህ በስተጀራባ ማረጃ ጎራዴህን ደብቀው ያዘው ጊዜ ሲፈቅድልህ ታርድበታለህ ነውና ነቅቶ ዘብ መቆሙ ይመረጣል።

ላለፉት 30 ዓመታት ኢሕአፓ ላይ ያልፃፈበት የሐሡት ድርሡት የለም ያልደረሡበት ጥቃት የለም ከውስጥም ከውጭም በአብዛኛ መልኩ ከውጭ የተሰነዘረበትን የሚሰዝርበትን ጥቃት ተቋቁሞታል ይቋቋመዋልም በርግጥ ጉዳት ደርሶበታል ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስበት ከውስጥ የተነሳው ጠላት ነው ለምሳሌ የ1969ኙ አንጃ ሻቢያ ወያኔ መኢሦን ደርግ ተደራርበው ካደረሱበት ጥቃት ጉዳት በላይ ነው በዛን ጊዜ የሊጉ አሻፈረኝ ማለት ኢሕአፓን ከትልቅ ውድመት አትርፎታል በ1970-71 ዓም በኢህአሠ ውሥጥ የተነሳው አንጃ ሠራዊቱ ጎዳው አንጃው በጠ.አ.ኮና በሠራዊቱ አባላት መካከል የነበረውን አለተማመንና አለመግባባት አጋኖ ቀረበ ጠ.አ.ኮው ይውረድ የሚለው ጥያቄ ጎልቶ መጣ ሻቢያና ወያኔ በኢህአሠ ውሥጥ ችግር መኖሩን አወቁ። ችግሩ ሳይወጣ ጦርነት አወጁበት ሰራዊቱ አሲንባን ለቆ እንዲወጣ ተገደደ ጠ.አ.ኮው አንጃ በተባሉ የተወሰኑ ግለሰቦች እርምጃ ወሰደ ጠአኮው በተቀጣጠለ እሳት ላይ ቤንዚል አርከፈከፈ አንጃው ያልጠበቀውን ድል አጎናጸፈ የተወሰኑ የድርጅቱ አባላት ትግራ ውስጥ ለወያኔና ለደርግ እጃቸውን ሰጡ እንዲሁም ኤርትራም እያለ ሠራዊቱ ብዙ ጓዶች ወደ ሱዳን ሄዱ ጠንካራ ጓዶች ብቻ ነበ\ሩ ጎንደር የደረሱ። ጎንደር በነበረውም ሰራዊትም ጠ.አ.ኮውን ያለማመን ችግር ነበር ችግሩን ለመፍታት ብሎ ጠ.ፓ.አ.ኮው ጠ.አ.ኮውን አፈረሰው በምትኩም በአባላት ምርጫ ጊ.አ.ኮ ይቋቋማል ተባለ አባላትም ተረጋግተ ትግላቸውን ቀጠሉ ጎንደር ውስጥ አራት ርጅን ተመሰረቱ ብዙ ድሎችን ኢህአሠ ተጎናጸፈ። ኢህአሠ መልሶ ኢህአሠ ሆነ ሁለት ርምጃ ወደፊት ሄደ እያለ በማናውቃቸው ሰዎች እንደነ ሰለሞን ገ/ስላሴ አምዴ እንዲሁም እነሱ መሰሎች ሌሎች ተጨምረው ጊአኮው ተመሠረተ ጊ.አ.ኮው በተመሰረተ ስድስት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ በሰራዊቱ ብተና ተካሄ የብተና ተወናዋይ የነበሩት የጊአኮ አባላት ናቸው።

የመርሻው አንጃ ስራውን የጀመረው ከኢዴሐቅ ምስረታ ጀምሮ ነው። በተለይ

የኢዴህቅ ሊቀ-መንበር ተብሎ በማዚያ ወር 1983 ዓም ሢመረጥ ከውቀቱ ከአቅሙ በላይ ልቡ አበጠ ሥራ ሁሉ እራሱ ማስተዋወቅ እኔ የጉራጌዪቱ ልጅ ማለት ጀመረ። የራሱን አድናቂዎቹ ማሰባስብ ጀመረ። መርሻ የተናገረው እግዚአብሄር የተናገረው ሆነ። የውጩን ኢሕአፓ የመዋቅር ተቆጣጠርኩ ብሎ አሰበ። ግን የመርሻ በውጭ አገር መንገሥ መቅለል ትርጉም የለሽ እንደሆነ ያውቀዋል። ምክኒያቱም ሜዳ ውስጥ ከሱ በላይ እውቀት ያላቸው በዕምነታቸው በጥንካሬአቸው ማንም የሚያውቃቸው የሚያከብራቸው የትግሉ የበኩር ልጆች ሜዳ ውስጥ እንደ ነበሩ ሰለሚያውቅ በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ቀርቦ ለቀረበለት ሰሎሞን ክፍሌ ጥያቄ ስለኢዴህቅ መመስረተ ከመመለስ ይልቅ የኢህአሠን እንቅስቃሴ ጎንደር ክፍለ አገረ ውስጥ የት የት እንደ ሚንቀሳቀስ ጎጃም ክፍለ አገር ውስጥ የት የት እንደ ሚንቀሳቀስ አጋለጠ መርሻ ባጋለጠው መሰረት ወያኔ በሻቢያ በሱዳን መንግስት እርዳታ በኢህአሠ ላይ ከበባ አካህደ ብጹህ የኢሕአፓ መሪዎች ተሰው ኢህአሠም ተደመሰሰ።የመርሻ የመጀመሪያው እቅዱ በአጥቂነት ተወጣ። ሁለተኛው አቅዱ ኢሕአፓን እሱን በሚያመቸው መንገድ የአገር ቤቱንም የውጩንም መዋቅር መቆጣጠር ኢሕአፓን እሱ ካልተቆጣጠረው ለማጥፋት ለመበተን ስሙን ይለወጥ የሚለው ጥያቄ እንዲነሳ አደረገ። ኢሕአፓን ለማጥፋት የ ኢሕአፓን ጉልበት ገንዘብ ኢዴህቅን ለሽፋን ተጠቀመ በኢዴህቅ ስም በየቦታው እየዞረ በ ኢሕአፓ ላይ ወንጀል የሰሩ ሠራዊቱን የበተኑ ግለሰቦቹን እንደ ሰሎሞን ገብረስላሴ ደሳለኝ ወይም ዶ/ር ዜሮ ጸሀየ እንዲሁም ሌሎች በ ኢሕአፓ መዋቅር ውስጥ እንደ ነበሩ ማንም የማታወቁ ግለሰቦች እንዲሁም የደርግ የፍስ ገዳይ ግለሰቦች እንደ ዘሪሁን ተሾመ ታከሎ ተሾመ ያሉት ሁሉ ወደ ኢሕአፓ ገቡ። አርማጭሆ የነበሩትን ሦስት ሀይሎች ድርጅቱ ፈርሷል ብሎ በትኖ ይዞት የነበው የድርጅቱን ገንዘብና መሳሪያ ሳያስረከብ ከድቶ ሱዳን የገባውን ሰለሞን ገ/ስላሴን እንዲሁም ሞት ለደብተራው ሞት ለ ኢሕአፓ ብሎ ወረቀት በትኖ የሄደውን ደሳለኝ ወይም ዶ/ር ዜሮ ተመልሰው የ ኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ውስጥ ገቡ።

ኢሕአፓን ለማፍረስ ትግሉ ተጀመረ በተለይ የአማራጭሆ ሀይሎች የሰላም ጉባኤ አዲስ አበበ እንዲሆን ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ መርሻ ህልምም ቅጀቱ የአዲስ አበበ ጉዞ ሆነ በኢዴህቅ ውስጥ እንግባ አንግባ ትርምስ ተጀመረ። ኢዴህቅ እንደ ኢዴህቅነቱ ለመግባት ወሰነ ኢሕአፓም እንደ ኢሕአፓነቱ እንደ ማይገባ ተወካይም እንደ ማይልክ ወሰነ። መርሻ አበደ። እናተ አትግቡ እኔ እንደ ኢዴህቅ ሊቀ-መበርነቴ እገባለሁ፤ ለደህነታችን መለስ ዜናዊ ሙሉጌታ አለምሰገድ ሰባት ነጋ

ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል እንዲሁም ጌታቸው አሰፋ ቃል ገብተዋል ብሎ አጉራ ዘሎ ጉዞውን ጀምሮ ካይሮ ደረሰ። ካይሮ አለም አቀፍ አይሮፕላን ውስጥ አያለ ባልታወቀ ምክኒያት አይሮፕላኑ አምልጦት ወደ አዲሥ አበበ ሄደ። በውኑ ተኝቶ የኢትዮጵያ ቦሌ አይሮፕላን ህዝቡ ተሰልፎ መርሻ! መርሻ! መርሻ! ሲል የተሰማው ድምጽ ቅዠት ሆነ። ከእሱ ጋር ተጉዞ የነበረው የባንዳና የአድርባይ መንጋ ወደ መጣበት ተመለሰ። መርሻ ጌታዋ የሞተባት ውሻ መስሎ መሄጃ አጥቶ እነ ኸርማ ኮን አሜሪካ ተመልሰህ አትገባም ብለውት አሎራ እያለ ብቻውን ሲያወራና ሲጮህ ዛሬ እንደ ጠላት የሚያየው ድርጅት የኢሕአፓ አባላት ናቸው ከካይሮ አይሮፕላን ማሬፊያ አውጥተው ወደሌላ አገር ሰድደው ከብዙ ውርደት ያዳኑት። ኢሕአፓ መርሻ አጉራ ዘሎ ነው የሄደ ብሎ አልተወውም። በሚቻለው ሁሉ እነ ኢያሱ አለማየሁ መከረውለታል እንደ ምንም ብሎ ካናዳ ሲደርስም አንድ የ ኢሕአፓ አባል አሁን በመሽጋን አካባቢ የሚኖር ካናዳ ድረስ በመሄድ በጠፍ ጨረቃ በሌባ መንገድ በኬሻ ጠቅሎ አሜሪካ እንዳ አመጣው ይታወቃል። መርሻ የ ኢሕአፓን እጁን አመድ አፋሽ አደረገው ኢሕአፓን ለማፍረሥ ሥራውን ቀጠለ ኢሕአፓን ለማጠናከር በሚል ሽፋን ኢሕአፓን የሚያፈርሥ ግብረ ሀይል ተቋቋመ። በመርሻ ሆነ የሚመራው ሙሉ ሁለት ዓመት እየሰባሰብሁኝ አሰባስቤአለሁ ብሎ እ.አ.አ 2007ዓ ም በዳላስ ከተማ ስብሰባ ተጠራ። የመጣው ሰው ቁጥር ሃያ ነበር 15ቱ የግብረ ሀይሉ ነብሩ የቀሩት አምስቱ ሁለቱ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ሲሆኑ ሶስትም ተራ ኢሕአፓ አባላት ነበሩ። የትአለ የተጣራ ሰው? ለምን አልመጣም? የሚል ጥያቄ ሲቀርብ እስቲበል የሚባል፤ በካናዳ የግብረ ሀይሉ ጋጃ መች ጥያቄውን ያቀረበውንና ጥያቄውን የደገፈውን ግለሰቦች ካልገደሁ ብሎ አዳራሹን ረበሸ። የግበረ ሀይሉ ውርደትን ክስረትን ተጎናጸፈ። ኢሕአፓም በቀላሉ ሊፈርስ እንደ ማይችል ማፍረስም እንደማይቻል መርሻ አውቆ ነበር። ነገር ግን የመጨረሻው ሙከራ ለአምስተኛው ጉባኤ ተዘጋጀ። እንደ ማይሳካላቸውም ሲያውቁ ቁርሳቸው ምሳቸውን እራታቸውንም በጉባኤ ስም በልተው ሰው ሳያያቸው የበሉት ሳይከፍሉ በለሊት አምልጠው ሄዱ። የቀሩትን በዕዳ አስይዞው ለዚህ ነው ከረኛ ጋር አትዋል ዞር ስትል ምሳህን ይበላብሃል የሚባለው። ይሄነው የሰለጠነ የፖለቲካ ማለት። ዲክታተሮቹን ሸውደዋቸው ሄዱ። የአገሬ ሰው ሲጸልይ እንደ ባለየ ሰው አደራህን በሆዴ እንዳ ታስገመግኝ እርኩስ ልጅ ከመውለደ ይሻላል ማስወረድም ይቻላልም።

ለምን ይሆን ይህ ያህል የታሪክ ግፋፎ ቆሻሻ ወደ ኢሕአፓ የሚገፋበት ለምን ይሆን? ይህን ያህል ውሸት በ ኢሕአፓ ላይ የሚዋሸው ለምን ይህ ያህል ካራ በ

ኢሕአፓ የሚሣልበት ምን በደለ? ምን አጠፋ? እያልሁ ከእራሴ ጋር ስከራከር ለካ መልሱ ቀላል ኑሯል። ኢትዮጵያን ለማጥፋት ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚለውን ክፍል መጀመሪያ ማጥፋት ነው ነበር ኒሯል እቅዳቸው አንድ ከክርስቶስ ልደት በፊት በቻይና አገር የነበረ ወታደራዊ ትምህት የሚያስተምር መምህር ሲያስተምር የጠላትህን ጠንካራና ደካማ ጎኑን አጥንተህ ጠላትህን በጠንካራ ጎኑን ውጋው ምታው በጠንካራ ጎኑ ተመቶ የወደቀ ጠላት መነሻ የለውም።ታጋዩ ጠንካራ ጎኑን በጥንካሬ መጠበቅ አለበት። አንዷ እጣትህ ከገማች ቆርጠህ ጣላት ሌሎችን ሳታገማብህ ከእንዲህ ከጠላት ከጠላት ጀሮ ጠቢ ጋር አብሮ መብላት መጠጣት ይቁም።የትላትናው እትብት እሱ ከበጠሰው አንተ አትጨነቅለት። ቃልኪዳን ሰብሮ የዛሬው ተውትና በትናቱ እንከባበር ማለት ትላንት ዛሬን ወለደ። ነገር ግን ዛሬ ትላንትን መውለድ ስለማትችል በዛሬው ሚዛን መመዛዘኑ ለትግሉም ለታጋዩም ጥራት የመጀመሪያው ስንቅና ትጥቅ ነው እላለሁ።

አቸናፊ አራጋው--ምንሽር